# PANORAMA # XXXIX

## የትዝብት አድማስ

ነሀሴ 23 2000 ዓም

## ጠፍተው የቀሩቱ

በየትኛውም ሀገር ይሁን በማነኛውም ዘመን፥ ለነፃነት፥ ለፍትኅ-ርትዕና ለዴሞክራሲያዊ መብት በግንባር ቀደም ተሰልፎ የተባ ትግል እየታገለ ተሰውቶ የሚያልፈው ከኅብረተሰቡ ክፍል በጣም ጥቂቱ ብቻ ነው፡፡ ለዚህም በቂ ምክንያት አለው፡፡ የጭቆናው ክብደት፥ የዴሞክራሲ ጥማትና የፍትኅ-ርትዕ ጉድለት ሁሉንም የሀገሪቱ ዜጋ ቢያንገፈግፈውም፥ ሁሉም በዕኩል ደረጃ ወደ ትግል ይሰማራል ተብሎ ስለማይጠበቅ ነው፡፡ ከኅብረተሰቡ ክፍል ውስጥ በግንባር ንቃተ-ኅሊናው ያዘጋጀውና የገፋፋው የትግሉን ገፈት ይቀምሳል፡፡ ማቄን ጨርቄን፥ ቤት ንብረቴን፥ ትዳር ቤተሰቤን፤ ጤንነት ሕይወቴን ሳይል ማነኛውንም ነገር ጠብ ዕርግፍ አድርጎ ለመስዋዕት የሚዘጋጀው ሁሉ አይደለም፡፡ ይሆናል ተብሎም አይጠበቅም፡፡ ነፃነት ማጣቱ፥ ፍትኅ መጓደሉ መላውን ዜጋ ቢነካውም ትግሉን እስከ መጨረሻ የሚገፋው ያው ቆራጥ ታጋዩና አመፀኛው “ የትግሉ ነው ሕይወቴ” ያለውና የቆረጠው ብቻ ነው፡፡

ልዩ ልዩ የኅብረት ሰብ ክፍል ሕይወቱን መምራት አለበት፡፡ ይህ ስለ ተባለ ግን ብዙሀኑ ጭቆናውን ተቀብሎ፥ ጨቋኞቹን ወዶ፥ በሥርዓታቸው ተስማምቶ ይኖራል ማለት አይደለም፡፡ በግድም ይሁን በውድ የሚጨቁነው ሥርዓት እንዲወገድለት ይሻል፡፡ በትግሉ ንቁ ተሳትፎ ሊያደርግ ባይችልም፤ እንደ ግንባር ታጋዮች ተመጣጣይ መሥዋዕት ባይከፍልም፥ መሥዋዕት ከፍለው ነፃ ሊያወጡት የሚታገሉትን አርበኞች ግን በግልፅም ይሁን በኅቡዕ

እንዳመቻቸው ይደግፋል ፤ ይተባበራል። ይህ በታሪካችን የታየ- የቆየ አሰራርና ልምድ ነበረ። ዛሬ ይህ አሰራር   ቀጥሏል አልቀጠልም ሌላ ጉዳይ ነው።

በኢትዮጵያ የረዥም ዘመን ታሪክ ውስጥ የካቲት 66 የተለየ ምዕራፍ አስመዝግቦ እንዳለፈ ማንም ኢትዮጵያዊ አይከራከርም። የነበረውን ሥርዓት በመቃወምም በሀገሪቱ አፅናፍ እስከ አፅናፍ ሆ! ብሎ  ተነስቶ ጨቋኙን አስተዳደር ለውጦታልም። ትግል መራራና ጎምዛዥ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን፥ ረዥምና አድካሚ ጉዞ የሚጠይቅም ጭምር  በመሆኑ ይኸው አሁንም ትግሉ አላቆመም። የገቡበትን ቃል ኪዳን ጠብቀው ታግለው የተሰዉቱም ሆነ በህይወት ያሉትም ለእዚህ ኅያው ምስክሮች ናቸው።  የተሰውቱን እያከበሩ የሚታገሉትን መደገፍና ማበረታታት ግን ከሁሉም ዜጋ የሚጠበቅ ነው። ነቅተውና ሕዝባቸውን አፍቅረው በግንባር ቀደም የታገሉት ግን የተለየ ፍዳና መከራ ለመቀበል  ከሌላው ዜጋ የበለጠና የተለየ ኃላፊነትም ሆነ ግዴታ  ማንም የሰጣቸው አልነበረም። ኅልቆ መሳፍርት ስቃይና መከራ ለመቀበልም ለእነርሱ ብቻ ያስረከባቸውና  ያወረሳቸው የለም ለሕዝብ ፍቅር ለሀገር ጥቅም፥ሲባል ብቻ በዓላማ ፀንቶ መታገል፥ ለአንድ ትውልድ ወይም፥ ብሔር፥ ወይም የኅብረተሰብ ክፍል ብቻ የሚተው ኃላፊነትና ግዴታ መሆን አይገባውም ። በግንባር ቀደም ታገለ አልታገለ፥ ማነኛውም ዜጋ ከጭቆና ለመላቀቅ ከፈለገ፥ የራሱን ድርሻ መወጣት እንደሚኖርበት ሌላ አስታዋሽና ጎስጓሽ፤ ሊያስፈልገው አይገባም። ኢትዮጵያ የጋራችን ነችና ሁሉም የበኩሉን መወጣት እንዳለበት አከራካሪ አይሆንም። ባይበገሬነት ትግሉን ሥራየ- ጉዳየ ብለው በመያዝ የቀጠሉት ኃይሎች ብቻ ሳይሆን፥ የገቡበትን ቃል ኪዳን ለመጠበቅና ትላንት በትግሉ ሜዳ የተሰውቱንም  የትግል ጓዶቻቸውንም አደራና ክብር ለመጠበቅም ጭምር ለመሆኑ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባ ያውቀዋል። ታጋዮቹም ተጠያቂነታቸውና ኃላፊነታቸው በቀጥታ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ በመሆኑ፥ ለማንም ሆነ ለምንም ደንታ የላቸውም። ሌላው አወቀላቸውም አላወቀላቸው  ትርጉም የለውም። ታሪክ ሰሪ ሰው እንጅ የተገላቢጦሹ ስለአይደለ፥ ታሪክ እየሰሩ ማለፍ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንግዳ አልነበረም። ታሪክን ለመተርጎም የሚጨነቀው ኅያው እንጅ ሰማዕታት ስለአይደሉ፤  እየተዋደቁ የተሰዉት ለከንቱ ውዳሴ ብለው ሳይሆን፥ ለሕዝባቸው ፍቅር፥ ለሀገራቸው ክብርና ለዓላማቸው ፅናት ብቻ ሲሉ  ነው።

በመሆኑም ኀያው፥ ገድለ-ታሪካቸው  መገምገም ያለበት፥ ከፍቅር ወይም ከጥላቻ ሳይሆን፥ ከኀሊና ወቀሳ ነፃ በሚያደረግ መስፈርትና ሚዛን ቢሆን ፈራጁን ውለታ ቢስ አያሰኘውም።

 የታጋዮችን ተግባር መገምገም ያገባኛል የሚል ኅብረተሰብ ደግሞ፥ በትግል የተሰውቱን ብቻ ሳይሆን፥ መዳረሻቸው የጠፋውንም ታጋዮች ጭምር የት እንደወደቁ መጠየቅና ማፈላለግ ግዴታና ኃላፊነት እንዳለበት ሊስተው አይገባውም። ከተሰውቱና  በወያኔ ወኀኒ ከሚማቅቁት ታጋዮች በስተቀር፥ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ዜጎች መዳረሻቸው የማይታወቅ እንዳሉ መገንዘብ የአንድ ሕዝብ ብሔራዊ ግዴታ መሆኑን መታወቅ አለበት።  ወያኔ  የኢትዮጵያ የሁልጊዜና ያመረረ ጠላት እንደሆነ መጀመሪያውኑ ተረድተው ወደ አዲስ አበባ እንደይገባ በግምባር ቀደም ሲፋለሙ የነበሩ ታጋዮች እስካሁን የት እንዳሉ የሚያውቅ የለም።  የሀገርም ሆነ የውጭ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ድርጅቶች፥ እነዚህን ዜጎች አስመልክቶ  ያደረጉት ሙከራ መኖሩን የኢትዮጵያ ሕዝብ አያውቅም።  እነኝህ መዳረሻቸው የጠፉ ታጋዮች የተጋለጡት፥ ወያኔን አምርረው በመዋጋታቸወና  አሁን ሀገራችን የወደቀችበትን ሁኔታ እንዳይደርስ አስቀድመው በመገንዘባቸው ነበር። ሌላ ምንም ወንጀል አልነበረባቸውም። የታጠቀውና የተደራጀው መደበኛ የሀገሪቱ ሠራዊት መሪ በማጣት በየቦታው በሚበታተንበት ወቅት እነኝህ፥ አሁን መዳረሻቸው የጠፉ ቆራጥ ታጋዮች፥ አምርረው የወያኔን ሠራዊት ተዋግተውታል። በየአሳቻው ቦታ እየዘለቁ ይህንን ከፋፋይ ኃይል ረፍርፈውታል፥ ርምጃውንም  ገትተውታል።

  በዚህ የቀውጢ ሰዓት በግንባር-ቀደም ሲዋጉ - ሲያዋጉ በጠላት እጅ ከወደቁትና እስካሁንም ድረስ በሕይወት ይኑሩ አይኑሩ ከማይታወቁት ውስጥ፥ እነ ፀጋየ ገብረመድኀን ደብተራው፥ ይስሐቅ ደብረፅዮን፥በለጠ አምሐ ፤ስጦታው ሁሴን፤ተክላይ ገብረ ስላሴ፤ሐጎስ በዛብህ፤ደሳለኝ አምሳሉና፡አዛናው ደምሌ ይገኙበታል። ወያኔም በተደጋጋሚ ተጠይቆ ምላሽ ለመስጠት ድፍረቱንም አላገኘም፤ ኃላፊነቱን አልወሰደም። አንዴ አልተያዙም ሌላ ጊዜ ደግሞ ተገድለዋል እያለ መቀለዱን መርጧል። ከእነዚህ ሌላ ደግሞ ወንዱ ሲራክ ደስታ፤ተስፋዬ ከበደ ፤ለማ ኃይሉ፤ አበራሽ በርታ፤ተሾመ በየነ፤ ሞት ባይኖር፤ ብርሀኑ እጅጉ፤ ደምሴ ተስፋዬ፤ ኢዮብ ተቀባ፤ጌትነት አስናቀ  ወዘተ በወያኔ ታስረው ደብዛቸው ጠፍቷል።

እነኝህ መዳረሻቸውን እስካሁን ማንም ያላወቀው የቁርጥ ቀን ታጋይ አርበኞች የኢትዮጵያ ሕዝብ አንጡ ራልጆች ናቸው። ወያኔንም የተፋለሙት በአንድ ዓቢይ ምክንያት ብቻ ነበር።ይኸውም በኢትዮጵያ የመኖርና ያለመኖር ጥያቄ ነው። ኢትዮጵያን ለማጥፋት እንደ አበደ ውሻ ሲባክን የነበረውን ዘረኛ ድርጅት እስከ መጨረሻ ጠብታ ደማቸው የተፋለሙትና አደጋ ላይ ሊወድቁ የበቁት፥ ሌላ አንዳችም ምክንያት አልነበራቸውም። ኢትዮጵያ መጥፋት የለባትም በማለታቸው ብቻ ነበር። ከሁሉ አስቀድሞ የወያኔን ዓላማና ዕኩይ ተግባር ያውቁ ስለነበር፥ ሕዝባቸው በዘር እንዳይከፋፈል፤ ሀገሪቱም እንዳትጠፋ ግምባር ቀደም ተጋድሎ አድርገው ይህ ነው የማይባል ጉዳት ደርሶባቸዋል። የት አሉ? ወዴት ወደቁ? ብሎ በመጠየቅ ትክክለኛውን መልስ ማግኘት ያለበት መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑን የታሪክና የዜግነት ግዴታ እንደሆነ መታወቅ አለበት። መዳረሻቸው የጠፋውን ልጆቹን አስመልክቶ የኢትዮጰያ ሕዝብ ወያኔን መጠየቁ የሞትና ሽረት ጉዳይ እንደሆነ ማንም ሊስተው የሚችል ጉዳይ አይደለም። ወያኔ ምላሽ ይሰጣል ባይባልም፥ ጥያቄው ግን ጎያው፥ ተከታታይና ተፅዕኖ የሚያደርግ መሆን አለበት።

ለሀገር አንድነት፥ ለሕዝብ ነፃነትና ለዴሞክራሲ ሲሉ የተሰውና ደብዛቸውም ስለጠፋ ዜጎች አለመቆርቆር ሰብዓዊ ባኅርይና ኅሊና የሚፈቅደው ነው ብሎ ለማመን ያስቸግራል። ከሀገሩ ጠላት ጋር ሲፋለሙ የተሰውቱንም ይሁን የጠፉትን ዜጎች መዳረሻ ፈልጎ ማግኘትና ቁርጡን ማወቅ የአርበኞችን ወረታ እንደመክፈል ይቆጠራል ብለን እናምናለን። ይህንን ማድረግ፥ ከሁሉም አኳያ ሲፈረጅ፥ ዕጥፍ ድርብ ጠቀሜታ ይኖረዋል ብለንም እናምናለን። በመጀመሪያ፥ የአርበኞችን ወረታ መክፈል የአንድን ሀገር ሕዝብ ታላቅነት ከማስመስከሩም በላይ፥ ለከፋዩ ዜጋ የሥነልቦናና የመንፈስ ደስታን ይሰጠዋል። ሁለተኛም አዳዲስ አርበኞችንና ታጋዮችን ለማፍራት ዕድል ይሰጣል። ለሚመጡት አርበኞችም በር ይከፍታል። ሦስተኛም የታጋዮችና የአርበኞችን የገድል ታሪክ እየተማረ ለሚያድገው አዲስ ትውልድ የማንነቱ መግለጫና የዜግነት ኩራቱ እንዲፋፋ ይረደዋል። አራተኛ የታጋዮችና የአርበኞች ቤተሰቦችና ዘመዶችን ሀዘን ያቃልላል። የተጨነቀውንም መንፈስ ያረጋጋል። በአጭሩ ጠቀሜታው በርካታ ነው። የተሰውለቱንና የት እንደወደ ያልታወቁትን አርበኞች ደብዛ ያልፈለገ ሕዝብ ልክ ዛሬም

እንደትላንቱ፥ “አ! አንቺ ኢትዮጵያ፥ የትላንቶቹን አርበኞች ከአልቀበርሻቸው በሻሸ፥ የሚተካው እንዳይሸሽ” መባሉ የሚቀጥል እንዳይሆን ልንሰጋ ይገባናል። ይህች ዘለዓለም የታሪክ ምፀት መጫወቻ የሆነች ሀገር፥ የገደላትን እያበላች፥ የተሰዋላትን እያስራበች፥ እያስከፋች መቀጠሏን መች እንደምታቆም ግራ ይገባናል። እስኪ ልብ እንበል! እነፀጋየ ገብረመድኅንን ደብዛቸውን እያጠፋች፥ እነመለስ ዜናዊን በቤተ መንግሥት ስጋጃ እያሽሞነሞነች ፥ እነ ገለብና መሐሪን ፣ ደረጀ፣ዋሲሁንና መስከረምን ለወያኔ ሰለባ በበረሐ ጥላ እነስብሐት ነጋን እያንደላቀቀች፥ ስንቱን ፀረ ወያኔ በቃሊቲና ሌሎች የምድር ሲኦሎች እያቆራመደች ያለች መሆኗን በቃ ብሎ ማመፅና ወንጀለኞቹን ለማስወገድ መታገል ሲገባ ጀግኖች ልጆቻችን የት ደረሱ ብሎ ጩኸት ማሰማት ደግሞ ፣የታቀውሞ ሰልፍ እያካሄዱ መጠየቅ ደግሞ ለታገሉልን ልናደርግ ከሚገባን በጣም አነስተኛው ነው።

እኛ ዛሬ ኢሕአፓ የተመሠረተበትን ሠላሳ ስድስተኛ የታወጀበትን 33ኛ ዓመት በምናከብርበት ዋዜማ፥ ለሀገራቸው አንድነት ለሕዝባቸው ነፃነትና ዴሞክራሲያዊ መብት መከበር ሲሉ ከወያኔ ጋር ሲፋለሙ መዳረሻቸው የት እንደሆነ ያልታወቀውን ጓዶቻችንና የሀገራችን አርበኞች የምናስታውስ መሪር ሀዘን በተመላበት ትካዜ ቢሆንም፥ በሌላ በኩል ደግሞ ግዳጃቸውን ተወጥተዋልና በኩራትም ነው። የእነርሱን የመጨረሻ ዕድል እስከምንረዳ ድረስም ፍለጋችን መቀጠል የትግላችን ዓይነተኛ ሂደት እንደሚሆን የወያኔ መሪዎች እየተጨነቁም ቢሆን ሊያውቁት ይገባል። ጠፍተው የቀሩቱ ሞት ሽረታቸውን ሳናውቅ የጎሊና ዕረፍት እንደማናገኝ ሁላችንም ጊዜ የማይሽረወው ቃል ኪዳን አለብን። ትግላችንንም በመቀጠል እናከብራቸዋለን፤ እናስታውሳቸዋለን።